ረ ፡ የሚያስረዳ ፡ ማስረጃ ፡ እያለ ፡ በኢትዮጵያ ፡ የመሠረተ ፡ ፊደል ፡ በካም ፡ ቤት ፡ ሲያያዝ ፡ የመጣው ፡ የፊደል ፡ ቅርጽና ፡ መጻሕፍቱ ፡ እያሉ ፡ ጥንታዊነታቸውን ፡ የሚያስረዳ ፡ ታሪክ ፡ ያለባቸው ፡ ከዓለም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መጻሕፍቶች ፡ ብልጫ ፡ ያላቸው ፡ መጻሕፍቶች ፡ እያሉ ፡ ያለ ፡ ፍርኃት ፡ የኢትዮጵያ መጻሕፍት ፡ ከጽርዕ፡ ወደ ፡ ግዕዝ ፡ ተገለበጠ ፡ ማለታቸው ፡ የሚገርም ፡ ነው ። የጽሑፋቸው ፡ መለያየት ፡ ባ፩ኛው ፡ አፋቸው፡ የፊደል ፡ ደረጃ ፡ ያደራጀ ፡ አባ ሰላማ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ጽፈዋል ። ደግሞ ፡ በ፪ኛው ፡ አፋቸው ፡ አባ ፡ ሰላማ ፡ መጻሕፍቱን ፡ ከጽርዕ ፡ ወደ ፡ ግዕዝ ፡ ገለበጠው ፡ ይላሉ ። እንግዲህ ፡ ከሁለቱ ፡ ቃሎች ፡ የትኛው ፡ ነው ፡ የሚጨበጠው ፡ ከጽርዕ ፡ ወገን ፡ አባ ፡ ሰላማ ፡ ሲሆን ከግዕዝ ፡ ወገን፡ማንን፡እናድርግ።አባ፡ሰላማ፡ግዕዝን፡ ከማን ፡ አመጣው ። የፊደሎችን ፡ ደረጃ ፡ ፯ ፡ አድርጎ ፡ አደራጀ ፡ የተባለው ፡ የጽርዓውያን ፡ ፊደል ፡ ደረጃ ፡ ፯ ፡ ናቸው ፡ ለማለት ፡ ያስደፍራል ፡ ይሆንን ፡ የፊደልን ፡ ደረጃ ፡ ፯ ፡ መሆን ፡ ከምን ፡ መሠረት ፡ አመጣው ፡ ያዲሲቱ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሰዎች ፡ ያለነሱ ፡ መጻሕፍትን ፡ የሚመለከት ፡ የለም ፡ ማለት ፡ ነው ። ምንም ፡ ሐሰቱን ፡ እውነት ፡ እውነቱን ፡ ሐሰት ፡ እናርግህ ፡ ብለው ፡ ቢደክሙ ፡ ቢያስጠኑ ፡ ትልቁን ፡ ያልተተከሉ ፡ ሸክላ ፡ ትንሽ ፡ ከፊያ ፡ እንደሚያፈርሰው ፡ የነሱንም ፡ ሥራ ፡ ፲፱ ፡ ዘመን ፡ የተሠራውን ፡ ፖለቲክ ፡ በትንሽ ፡ ቀለም፡ ፍርስርስ ፡ አደርገዋለሁ ።

የኢትዮጵያን ፡ ፊደል ፡ እኛ ፡ እናውቀዋለን ፡ ሲሉ ፡ አለማፈራቸው ፡ በጣም ፡ ያስገርማል ። በነሱ ፡ ቤት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ፊደል ፡ አስደናቂ ፡ ምሥጢር ፡ የለበትም ፡ ተብሏል ። የፊደልን ፡ ምሥጢር ፡ መርምረው ፡ አውቀው ፡ ቢሆን ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ መሠረት ፡ የሌለው ፡ ነገር ፡ ባልጻፉ ፡ ነበር ። የፊደል ፡ መሠረት እንዲሁ ፡ በዘፈቀደ፡የሚነገር ፡ አይደለም ። ስለ ፡ ፊደል ፡ ምሥጢር ፡ ግዕዝና ፡ የእብራውያን ፡ ፊደል ፡ ለየብቻ ፡ ናቸው።የግዕዝ ፡ ደረጃዎቹ ፡ ፯ት ፡ ናቸው ፡ እነዚህም ፡ በ፯ቱ ፡ ዕለታት ፡ ሀ ፡ ግዕዝ ፡ እኁድ ፡ ሁ ፡ ካዕብ ፡ ሰኑይ ፡ ሂ ፡ ሣልስ ፡ ሠሉስ ፡ ሃ ፡ ራብዕ ፡ ረቡዕ ፡ ሄ ፡ ኃምስ ፡ አሙስ ፡ ህ ፡ ሳድስ ፡ ዓርብ ፡ ሆ ፡ ሳብዕ ፡ ቀዳም ፡ እንደዚህ ፡ እያሉ ፡ ሲሄዱ ፡ ዘወትር ፡ በግዕዝ ፡ ፊደሎችና ፡ ዕለተ እኁድ ፡ አይለያዩም ፡ በሄኖክ ፡ በመጽሐፍ ፡ በሚጠተ ፡ ብርሃናት ፡ እንደ፡ ሚሰፈረው ፡ ሚያዝያ ፡ እኁድ ፡ ሀ ፡ ሰኑይ ፡ ሁ ፡ ሠሉስ ፡ ሂ ፡ ረቡዕ ፡ ሃ ፡ ሐሙስ ፡ ሄ ዓርብ ፡ ህ ፡ ቀዳም ፡ ሆ ፡ በዚህ ፡ ሂሳብ ፡ ፳፯ቱ ፡ ፈደሎች ፡ በ፯ሲበዙ ፡ ፻፹፱ት ፡ ይሆናሉ ፡ ይህም ፡ በሄኖክ ፡ ሚዛን ፡ ሲመዘን ፡ ፩ኛ ፡ ሚያዝያ ፡ እሑድ ፡ ይብታል ፡ ፴ ፡ ፪ኛ፡ ግንቦት፡ ማክሰኞ፡ ይብታል፡ ፴፡ ፫ኛ፡ ሰኔ፡ ሐሙስ፡ ይብታል፡ ፴፩ ፡ ፬ኛ ፡ ሰኔ ፡ ሐምሌ ፡ እሑድ ፡ ይብታል ፡ ፴ ፡ ፭ኛ ፡ ነሐሴ ፡ ማክሰኞ ፡ ይብታል ። ፴ ፡ ፮ኛ ፡ መስከረም ፡ ሐሙስ ፡ ይብታል ፡ ፴፩ ፡ ፯ኛ ፡ ጥቅምት ፡ እሑድ ፡ ይብታል ፡ ፴ ፡ ፰ኛ ፡ ኅዳር ፡ ማክሰኞ ፡ ይብታል ፡ ፴ ፡ ፱ነኛ ፡ ታኅሣሥ ፡ ሐሙስ ፡ ፴፩ ፲ኛ ፡ ጥር ፡ እሑድ ፡ ይብታል ፡ ፴ ፡ ፲፩ ፡ የካቲት ፡ ማክሰኞ ፡ ይብታል ፡ ፴ ፡ ፲፪ኛ ፡ መጋቢት ፡ ሐሙስ ፡ ይብታል ፡ ፴፩ ፡ ጥቅል ፡ ድምር ፡ ልክ ፡ ፫፻፷፬ ፡ እንደዚህም ፡ የሆነ ፡ በመንፈቁ ፡ ፳፯ቱ ፡ ፈደሎች ፡ በ፯ት ፡ ሲበዙ ፡ ፻፹፱ ፡ ይሆናል ፡ ከቀኖቹ ፡ ጋር ፡ ሲመዘኑ ፡ ግዕዝ ፡ ግዕዙ ፡ እሑድ ፡ ሳብዕ ፡ ቀዳም ፡ እየተባለ ፡ ሲመዘን ፡ ፻፹፱ ፡ ቀኖች ፡ ከ፻፹፱ቱ ፡ ፈደሎች ፡ ጋር ፡ ልክ ፡ ይሆናሉ ። ደግሞ ፡ መልሶ ፡ ለመንፈቁ ፡ እንደዚሁ ፡ ሲመዘን ፡ ፈደሎችም ፡ ቀኖችም ፡ ፻፹፱ ፡ ይሆናሉ ሲደመሩ ፡ ፫፻፸፰ ፡ ይሆናሉ ። ይህንም ፡ ፫፻፸፰ ፡ ለ፯ት ፡ ሲመድቡት ፡ ፶፬ት ፡ ይሆናል ፡ በዚህ ፡ መሠረት ፡ እስከ ፡ ፯ት ፡ ዓመት ፡ ሲቆጠር ፡ ቀደም ፡ ሰንበት ፡ ብቻ ፡ ከ፯ቱ ፡ ዓመቶች ፡ ውስጥ ፡ ፯ት ፡ ፶፬ ፡ ፫፻፸፰ ፡ ይሆናል ። ይህም ፡ ፩ድ ፡ ንዑስ ፡ ሰንበት ፡ ይባላል ። በዚህ ፡ ሂሳብ ፡ እስከ ፡ ፵፱ ፡ ዘመን ፡ ሲቆጠር ፡ ከ፵፱ኙ ዓመቶች ፡ ፯ት ፡ ንዑስ ፡ ሰንበት፡ ይገኛል ። ከዚህም ፡ ከሰባቱ፡ ዓመቶች፡ ውስጥ ፡ ፯ት ፡ ጊዜ ፡ ፶፬ት ፡ ይገኛል ። ይህም ፡ ሲደመር ፡ ልክ ፡ ፫፻፸፰ ፡ ይሆናል ፡ ይ

እንዳደረጉት ፡ የጥንቱ ፡ ባለርስት ፡ እንደተነቀለ ፡ ነው ። አሁንም ፡ እነሱ ፡ እን ደልባቸው ፡ ከመስበክ ፡ አልቦዘኑም ። የትምርት ፡ ቤታቸውን ፡ እንደልብ ፡ ያስ ፋፉሉ ። ምንም ፡ ቢሆን ፡ የጠላት ፡ አስተማሪ ፡ መልካም ፡ መስሎ ፡ እንዳይታ ይ ፡ ጌታችን ፡ በቅዱስ ፡ ወንጌል ፡ አስጠንቅቆናል ። ዮሐንስ ፡ ፲ ፡ ፲፪ ፡ ወአሳብ ሰ ፡ ዘኢኮነ ፡ ኖላዊ ፡ ወዘኢኮና ፡ ዘዚአሁ ፡ አባግዕ ። ይህ ፡ ቃል ፡ ለኛ ፡ ማስጠን ቀቂያ ፡ ነበር ፡ ግን ፡ ለማን ፡ ያስባል ፡ የሮማ ፡ ልዑካን ፡ አስቀድሞ ፡ ዝምሮ ፡ አሳባቸው ፡ ሁሉ ፡ በረቂቅ ፡ ስብከት ፡ የሕዝቡን ፡ ልብ ፡ ለመሳብ ፡ ስለሆነ ፡ የ ወጣቶችን ፡ ልብ ፡ ባይመርዙብን ፡ በጣም ፡ የተሻለ ፡ ነበር ። የነሱ ፡ ስብከት ፡ በ ዛሬው ፡ ሰዓት ፡ በጣም ፡ አስጊ ፡ ነው ። ነገርን ፡ ማየት ፡ ባለፈው ፡ ዘመን ፡ ሁሉ የሠሩትን ፡ እኛም ፡ አንረሳውም ፡ ቀኑ ፡ የራቀውን ፡ ብንረሳ ፡ በቅርብ ፡ ቀን ፡ የ ተደረገውን ፡ አንዘነጋም ፡ ማለት ፡ ጥንታቂን ፡ ማስታወስ ፡ ነው ። በኛ ፡ በኩል በማንኛውም ፡ ምክንያት ፡ የሞቱትን፡ወገኖቻችንን፡ በመዝገብ፡ እያሰፈርን፡ ጉዳ ታችንን ፡ እያስታወስን፡ለፈጣሪአችን ፡ እያዘን ፡ እያመለከትን ፡ ያለነውም ፡ እየ ተስማማን ፡ ብንቀመጥ ፡ እንደምን ፡ አገራችን ፡ በቀናች ፡ ነበር ። እነሱ ፡ እንደ ኛ ፡ አይደሉም ፡ የሀገራቸውና ፡ የወገናቸው ፡ ነገር ፡ በጣም ፡ ስለሚጠናባቸው ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ መጥተው ፡ የሞቱትን ፡ ወገኖቻቸውን ፡ ልክ ፡ በአሕዛብ ፡ እ ጅ ፡ ስለ ፡ ሃይማኖት ፡ የሞቱ ፡ እያስመሰሉ ፡ ስሙንም ፡ እየመዘገቡ ፡ እያስቀመ ጡ ፡ የነዚያን ፡ ሰዎች ፡ ሞት ፡ እንደ ፡ ሰማዕት ፡ ሞት ፡ እያደረጉ ፡ በቀላቸውን ፡ ለመመለስ ፡ የማይዘነጉ ፡ ሰዎች ፡ ናቸው ። እነሱ ፡ ከአፍሪካ ፡ ካልወጡ ፡ ኢትዮ ጵያ ፡ ጤና ፡ ታገኛለች ፡ ማለት ፡ ከንቱ ፡ ነው ። በነሱ ፡ ምክንያት ፡ የሞቱትን ፡ ሰ ዎች ፡ ድምር ፡ ከላይ ፡ በመጠኑ ፡ ጽፌው ፡ ነበር ፡ ግን ፡ ወደ ፡ ሊቢያ ፡ ኢጣል ያኖች ፡ ለጦርነት ፡ እየቀጠሩ ፡ እየወሰዱ ፡ እዚያ ፡ እያዋጉ ፡ ያስፈጇቸው ፡ ሰዎች ቁጥር ፡ በግምት ፡ ከ፶ና ፡ ከ፰ሺ ፡ አያንሱም ፡ ፪ኛ ፡ በውጋዴንም ፡ በኩል ፡ በየጊ ዜው ፡ በሚነሳው ፡ ጦርነት ፡ ሁሉ፡ ያለቀው ፡ ሲገመት ፡ ካ፺ሺ ፡ አያንስም ፡ ከላ ይ ፡ እየተደመረ ፡ ከመጣው ፡ ኢጣልያኖች ፡ ምጽዋን ፡ ከረገጡ፡ አንስቶ ፡ የዓድ ዋ ፡ ጦርነት ፡ መጨረሻ ፡ ፪፻፶፰ሺ ፡ ፪፻ ፡ ይሆናል ። እንደዚህ ፡ ስለተባለ ፡ ለጠላ ትም ፡ ተቀጥረው ፡ የሞቱት ፡ ተጨምሮ ፡ ታስቦ ፡ ነው ።

፪ኛ ፡ ከ፲፱፻፳፯፡ ዓ፡ም፡ እስከ፡ ፴፩፡ ዓ፡ ም፡ ከላይ፡ እንደተጻፈው፡ በዋናዎች፡ ጦርነት፡ቦታና፡ደግሞ፡በየጊዜው፡በማናቸውም፡ምክንያት፡እርስበርሱ፡የተላለቀው በግምት፡ ፺፶ሺ፡ ይሆናል ። ይህ ፡ ሲደመር፡ ፬፻፰ሺ፻፪ ፡ ነው።ይህን፡ ያህል፡ ወገን፡ አልቆብን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኖች ፡ ተቃጥለውብን ፡ ያባቶቻችን ፡ መሳሪያዎች ፡ ሁሉ ፡ ተዘርፈውብን ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ የመከራ ፡ ጕርፍ ፡ በላያችን ፡ ላይ ፡ አልፎ ብን ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ ታሪክ ፡ ረስተን ፡ ያመጣብንን ፡ መርምረን ፡ ሳንረዳ ፡ መቀ መጣችን ፡ በጣም ፡ ያስደንቃል። የሞቱትን፡ ወገኖቻችንን ፡ ቁጥር፡ ባ፲፰ ፡ ዓመ ት ፡ በቀላል ፡ ግምት ፡ ፩ ፡ ሚሊዮን ፡ አይሆንም ፡ ነበርን ። ሞት ፡ የማይቀንሰው የለም፡ እነሱ፡ ከገቡ፡ ወዲህ፡ ኢትዮጵያ፡ እያደረች፡ ከማነስ፡ በተቀር፡፩ድ ፡ትርፍ፡ አላገኘችም፡ ነገሥታቷ ፡ መሳሪያ፡ እናስመጣለን፡እያሉ፡ይዋዋሉና ፡ ሃይማኖታቸ ውን ፡ አስከደውም ፡ ፩ድ ፡ መሳሪያ ፡ ለነ ፡ አጼ ፡ ሚናስ፡ ለነ፡ አጼ፡ ያዕቆብ፡ ለነ አጼ ፡ ዘድንግል ፡ ላጼ ፡ ሱስዮንስ ፡ ለነዚህ ፡ ሁሉ ፡ ያመጡት ፡ መሣሪያ፡ የለም፤ እንዲሁ ፡ በቀጠሮ ፡ ነገ ፡ ይመጣል ፡ ከነገ ፡ ወዲያ ፡ ይመጣል ፡ እየተባለ ፡ ነው ። ለወደፊቱ ፡ እንዲመከርበት ፡ ያስፈልጋል ፤ ከጦርነቱ ፡ በፊት ፡ የነበረ ፡ የስብ ከት፡ ዓይነት፡ አሁን፡ ደግሞ፡ ሲታይ፡ እንቅልፍ፡ ያስወስዳልን፤ምነው፡ እንቅልፍ፡ በዛ ። የወንድሞቻችንስ ፡ ደም ፡ አይወቅሰንም ፡ ማለት ፡ ይሆንን። ወገንን፡ መው ደድ ፡ ክቡር ፡ ሥራ ፡ ነው ። ጤሞቴዎስ ፡ ፭ ፡ ፰ ፡ ወዘሰ ፡ ኢይሄሊ ፡ ለቤቱ ፡ወይ ገድፍ ፡ አዝማዲሁ ፡ ውእቱ ፡ ክህደ ፡ ሃይማኖቶ ፡ ወየአኪ ፡ እምዘኢየአምን ፡ ለ ራሴ ፡ ብቻ ፡ ተመቸኝ ፡ ብሎ ፡ ከወገኖቹ ፡ ገዳይ ፡ ጋራ ፡ አብሮ ፡ እየበላ ፡ እየጠ


ደቂቁ ፡ ለካም፡ በበዘመዶሙ ፡ ወበበነገሮሙ ፡ ወበበብሔሮሙ ፡ አሕዛቢሆሙ ።
የካምን ፡ ዘሮች ፡ ከ፮ ፡ ቁጥር ፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ ፳፩ ፡ ቁጥር ፡ ይገኛል ። ፳፩ ፡ ወ
ለሴም ፡ ተወልዱ ፡ ሎቱ ፡ ኤላም ፡ ወአሶር ፤ ወአርፋክስድ ፡ ወሉድ ፡ ወአራም ፡
፭ ፡ ናቸው ፡ ወደቂቀ ፡ ኤላም ፡ ኤላህ ፤ ዮምኤል ፤ ያቴር ፤ ሞሶህ ፤ ፬ ፡ ናቸው ፡ ወ
አርፋክስድ ፡ ወለዶ ፡ ለቃይናን ፡ ወቃይናን ፡ወለዶ፡ ለሳላ። ወሳላ፡ ወለዶ፡ለዔቦር
ወዔቦር፡ ወለዶሙ ፡ ለፋሌቅ፡ ወለዮቅጣን። ከአዳም፡ ዠምሮ ፡ እስከ ፡ፋሌቅ፡ በት
ውልድ ፡ ፲፮፡ ትውልድ ፡ ነው ። በዘመን ፡ ከ፪ ፡ ሺ ፡ ፯፻ ፡ አይበልጥም ።

፳፮ ፡ ወዮቃጤን ፡ ወለዶ ፡ ለኤልሞዳድ ፤ ወለሴሌፋ ፤ ወለሴሌራሞት ፡ ወ
ለኢራኅ ። ፳፯ ፡ ወለሐይራ ፤ ወለኤዜላ ፤ ወለዴቂላ ፤ ፳፰ ፡ ወለዑባላ ፤ ወለአቢ
ማኤል ፤ ወለሳባ ፡ ፳፱ ፡ ወለሑፋር ፤ ወለሔዊላ ፡ ወለኢዮቦር ። ወኵሎሙ ፡ ደቂ
ቁ ፡ ለዮቃጤን ፤ ፴ ፡ ወኮነ ፡ ምንባራቲሆሙ ፡ እምነ ፡ ማሴ ፡ እስከ ፡ ሳፌራ ፡ ይበ
ጽሕ ፡ ደብረ ፡ ሰረቃዊ ፡ ፴፩ ፡ እሉ ፡ እሙንቱ ፡ ደቂቁ ፡ ለሴም ፡ በበነገዶ
ሙ ፡ ወበበነገረ ፡ ብሔሮሙ ፡ ወበበአዝማዲሆሙ ፡ ፴፪ ፡ ወዛቲ ፡ ይእቲ ፡ ነገደ ፡
ደቂቁ ፡ ለኖኅ ፡ በበዘመዶሙ ፤ ወእምነ ፡ እሉ ፡ ተወልደ ፡ ዘተዘርወ ፡ እምድ
ኅረ ፡ አይኅ ። እስከዚህ ፡ ድረስ ፡ ከባቢሎን ፡ ግምብ ፡ መፍረስ ፡ አስቀድሞ ፡
ያሉትን ፡ ነው ፡ ያመለከተ ። ከተካፈሉም ፡ በኋላ ፡ ያለውን ፡ ግን ፡ ም ፡ ፲፩ ፡ ፩
ወኮነ ፡ እምድኅረ ፡ ተንሥኡ፡ እምጽባሕ ። ከምሥራቅ ፡ ከተነሡ፡ በኋላ ፡ ዱር ፡ አ
ገኙና ፡ በዚያ ፡ አድረው ፡ የጡብ ፡ ረኸም ፡ ቤት ፡ እንሥራ ፡ ብለው ፡ ምክር ፡
ዠመሩ ፡ ብሎ ፡ ያመጣዋል ። በዓለም ፡ የተዘሩ ፡ አባቶች ፡ መሠረት ፡ ይህ ፡ ነው
ግን ፡ ይህ ፡ በኦሪቱ ፡ እንደተጻፈው ፡ ስለሆነ ፡ ፫ቱ ፡ አባቶች ፡ ሴም ፡ ካም ፡ ያፌ
ት ፡ ዓለምን ፡ በዕጣ ፡ እንደተካፈሉ ፡ የሚአስረዳ ፡ ወሰኑንም ፡ ሁሉ ፡ እየለየ ፡ የ
ሚአሳይ ፡ ኩፋሌው ፡ ነው ። የዓለም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሰዎች ፡ መጽሐፈ ፡
ሄኖክንና ፡ መጽሐፈ ፡ ኩፋሌን ፡ ደግሞ ፡ ፲፬ት ፡ መጻሕፍቶችም ፡ እሉ ፡ እነዚህ
ን ፡ ሁሉ ፡ አንቀበልም ፡ ስለሚሉ ፡ የዓለምን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሰዎች ፡ ፪ት ፡
አርስቶች ፡ አምልጠዋቸው ፡ ይኖራሉ ። ፩ኛው ፡ መላእክት ፡ መኖራቸውን ፡ የ
ሚአምኑ ፡ ሲሆኑ ፡ መላእክት ፡ ተፈጠሩ፡ የሚለውን ፡ ጽሑፍ፡ያለበትን ፡ ሳያው
ቁት ፡ ይኖራሉ ። ፪ኛው ፡ ይህን ፡ ዓለም ፡ ኖኅ ፡ ለ፫ት ፡ ልጆቹ ፡ በዕጣ ፡ እንደ ፡ ተ
ካፈሉ ፡ በቃል፡ አውሮፕን፡ለያፌት፡ እሥያን ፡ ለሴም። አፍሪካን ፡ለካም ፡ ነው ።
ማለትን ፡ በድምፅ ፡ ከመስማት ፡ በተቀር ፡ ፫ቱ ፡ አባቶች ፡ እንደተካፈሉ፡
ከነወሰኑ ፡ ተለይቶ ፡ የተጻፈውን ፡ መሠረት ፡ አምጡ ፡ ብሎ ፡ ቢጠይቁአቸው ፡
ኩፋሌውን ፡ ስለነቀፉ ፡ ለማስረዳት ፡ አይችሉም ። የአውሮፓ ፡ ሊቃውንት ፡
የአይሁድን ፡ ምክር ፡ እናከብር ፡ ብለው ፡ በኢትዮጵያ ፡ የሚገኙትን ፡ መጻሕፍ
ት ፡ አንቀበልም ፡ ብለው ፡ ባይተዋቸው ፡ ኑሮ ፡ ለትርጓሚው ፡ ሁሉ ፡ እንደም
ን ፡ ያለ ፡ ብርሃን ፡ ምንገድ ፡ በሰጣቸው ፡ ነበር ፡ እያልኩ ፡ ዘወትር ፡ ከማዘን ፡ አ
ላቋርጥም ። ስለዚህ ፡ አሁንም ፡ ከላይ ፡ እንደ ፡ ተጻፈው ፡ የኦሪቱን ፡ ብቻ ፡ ብጽ
ፈው ፡ በሰፊው ፡ የዙሪያውን ፡ ወሰን ፡ ሁሉ ፡ ለይቶ ፡ ስለማያስረዳ ፡ ለወገኖቼ ፡
መርጃ ፡ እንዲሆን ፡ በኩፋሌው ፡ የተጻፈውንም ፡ ከዚህ ፡ አስከትየ ፡ እጽፋለሁ
ኩፋሌ ፡ ፱ ፡ ፩ ፡ በቅድሜሁ ፡ በቀዳሚ ፡ ዘ፩ ፡ ዓመት ፡ ዓመተ ፡ ሱባዔ ፡ እንዘ ፡ ይ
ነብር ፡ ፩ዱ ፡ እምኔነ ፡ ተፈኖነ ፡ ኀቤሆሙ ፡ ወጸወዐ ፡ ደቂቀ ፡ ወቀርቡ ፡ ኀቤሁ
እሙንቱ፡ ወውሉዶሙ፡ወከፈለ ፡ ምድረ፡ በዕፃዊ ፡ ዘይእኀዙ ፡ ፫ቱ፡ውሉዱ ፡ ፪፡ ወ
ሰፍሑ ፡ እደዊሆሙ ፡ ወነሥኡ፡ መጽሐፈ ፡ እምሕፅነ ፡ ኖኅ ፡ አቡሆሙ ፡ ወወጽ
አ ፡ በመጽሐፍ ፡ ዕፃሁ ፡ ለሴም ፡ ማዕከለ ፡ ምድር ፡ ዘይእኀዝ ፡ በርስቱ ፡ ወበው
ሉዱ ፡ ወበትውልድ ፡ ዘለዓለም ። እማዕከለ ፡ ደብረ ፡ ራፋ ፡ እሙፃእ ፡ ማይ ፡ እም
ፈለገ ፡ ጤና ። ፫ ፡ ወየሐውር ፡ መክፈልቱ ፡ መንገለ ፡ ዓረብ ፡ እንተ ፡ ማዕከሉ ፡ ለ
ዝ ፡ ፈለግ ፡ ወየሐውር ፡ እስከ ፡ ሶበ ፡ ይቀርብ ፡ ኀበ ፡ ማየ ፡ ቀላያት ፡ ወእምኀ

ክሙ ፡ ወእፎኑ ፡ ኮኑ ፡ መጻሕፍተ ፡ ነቢያት ፡ ዘአበዊነ ፡ ወዘአበዊክሙ ፡ ውዕያ
ኑ ፡ እመ ፡ ጼዋዌ ፡ በእሳት ፡ አው ፡ ድኑናን ፡ ሀለዋ ፡ ወእፎ ፡ ሀለውክሙ ፡ አን
ትሙ ፡ ደቂቀ ፡ ፳ኤል ፡ ወደቂቀ ፡ ነቢያት ። ሰገድክሙኑ ፡ ለጣዖታተ ፡ አረማው
ያን ፡ ወለመላእክተ ፡ ባእዳን ፡ ወእፎ ፡ ኮንክሙ ፡ ሠዓርክሙኑ ፡ ሰንበታቲሁ ፡ ለእ
ግዚአብሔር ። ወእምድኅረዝ ፡ ሶበ ፡ ሰምዑ ፡ ዘንተ ፡ መልእክተ ፡ ዘአበዊነ፡ አን
ከሩ ፡ ወይቤሉ ፡ ንህነሰ ፡ ሀለውነ ፡ በዳኅና ፡ በጸሎተ ፡ ዳንኤል ፡ ወአዛርያ ፡ ወአ
ናንያ ፡ ወሚሳኤል ፡ እንዘ ፡ የዓቅበነ ፡ አምላክነ ፡ አምላከ ፡ አብርሃም ፡ ይስሐቅ ፡
ወያዕቆብ ፡ አንትሙኒ ፡ አሪገክሙ ፡ ኅሥሥዎን ፡ ለመጻሕፍተ ፡ ሕገ ፡ ሙሴ ፡ ወ
ዘ ፡ ዘነቢያት ፡ ንሕነሰ ፡ ሐለውነ — ፡ ሀገረ ፡ ጼዋዌ ፡ ወአንትሙሰ ፡ ውስተ ፡ ሀ
ገረ ፡ ማህል ፡ ወዛህን ፡ ባሕቱ ፡ ንሥኡ ፡ ዘንተ ፡ መጽሐፈ ፡ ዘኮነ ፡ እምኀበ ፡ አ
ብ ፡ ዳንኤል ፡ ነቢይ ። ወዘይቤ ፡ ዘንተ፡ ነገረ ። መጽአ ፡ ኀቤሆሙ ፡ ለአበዊነ ፡
እመጽሐፈ ፡ ትንቢቱ ፡ ለዳንኤል ፡ በዕደ ፡ ፭ዱ፡ ተንባላታዊ፡ ዘተፈነወ፡ እምንጉ
ሥ ፡ ኢትዮጵያ ፡ አይሱር ፡ ኀበ ፡ ዳርዮስ ፡ ንጉሥ ፡ ፋርስ ፡ ወሜዶን ፡ ዘይቤ ፡ ዳን
ኤል ፡ ነቢይ ፡ እንዘ ፡ እገብር ፡ ጸሎተ ፡ ወእትነኀይ ፡ ኃጣውእየ ፡ ቅድመ ፡ እግዚ
አብሔር ፡ መጽአ ፡ ኀቤየ ፡ ገብርኤል ፡ ወለመጽሐፈ ፡ ዝኒ ፡ ነገር ፡ ደመርዋ ፡
ምስለ ፡ መጽሐፈ ፡ ኦሪተ ፡ ሙሴ ፡ ዘመጽአ ፡ እምኢየሩሳሌም ፡ በዘመነ ፡ ሰሎሞ
ን ፡ ምስለ ፡ አበዊነ ፡ ቀደምት ፡ ወምስለ ፡ ኦሪተ ፡ ሙሴ ፡ ዘይቤ ፡ ሰዱሰ ፡ ዕለ
ተ ፡ ተገበር፡ ግብረከ ፡ ወበሳብዕ ፡ ዕለት ፡ አዕርፍ ፡ ወእምድኅረዝ ፡ መጽአ ፡
ቃለ ፡ ዳንኤል ፡ ነቢይ ፡ ለአበዊነ ፡ ተሐንጸት ፡ ኢየሩሳሌም ፡ በዘመነ ፡ ዘሩባቤል
ወተመይጡ ፡ ጼዋ ፡ ፳ኤል ፡ ውስተ ፡ ሀገሮሙ ። ወበውእቱ ፡ መዋእል ፡ ሖሩ ፡
አበዊነ ፡ ኀበ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ እስመ ፡ ለአከ ፡ ዘሩባቤል ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ ኀበ ፡
ንጉሥ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሰላመ ፡ እግዚአብሔር ፡ የሃሉ ፡ ምስሌከ ፡ ስምዓኒ ፡ በይነ፡
እግዚአቤሔር ፡ ዘሰአልኩከ ፡ ወፈኑ ፡ ሊተ ፡ በቅዱስ ፡ ስሙ ፡ ለአምላከ ፡ አበዊነ
፳ኤላውያን ፡ አማኅፀንኩከ ፡ እስመ ፡ መጽሐፈ ፡ ኦሪተ ፡ ሙሴ፡ በጽሐ ፡ ውስተ ፡
ሀገርከ ፡ እምቅድመ ፡ ጥፍአታ ፡ ለኢየሩሳሌም ፡ በእደ ፡ እምሔውከ ፡ ወልደ፡
ሰሎሞን። አንኒ ፡ እፌኑ ፡ ለከ ፡ ዘኮነ ፡ እምኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ መጻሕፍተ ፡ ነቢ
ያት ፡ ሀገረ ፡ ባቢሎን ፡ ወቂሮስ ፡ ዘጻሐፍዎ ፡ ትሩፋኒሆሙ ፡ ለነቢያት ፡ ቀደም
ት ፡ አንተሂ ፡ ፈኑ ፡ ሊተ ፡ እመጻሕፍተ ፡ ነቢያት ፡ እለ ፡ ይቀድሙኒ ፡ ወእምቅድ
መ ፡ ጥፍአታ ፡ ለኢየሩሳሌም ፡ ዘነበሩ ፡ እመናብርተ ፡ አበዊከ ፡ ከመ ፡ ይኩኑነ ፡
ተስፋ ፡ በኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላከ ፡ አበዊነ ፡ ሊተሂ ፡ ወለከ ። ወዘንተ ፡ ሰ
ሚአ ፡ ንጉሥ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ጸውዖሙ ፡ ለአበዊነ ፡ ወይቤሎሙ ፡ ንሥኡ፡ መጽሐ
ፈ ፡ ኦሪት ፡ ዘሙሴ ፡ ወዘኢያሱ ፡ ወሳሙኤል ፡ ወዘመሳፍንት ፡ ወመዝሙረ ፡ ዳ
ዊት ፡ ምስለ ፡ መጽሐፈ ፡ ነገሥት ፡ ወመጽሐፈ ፡ ሰሎሞን ፡ ሑሩ ፡ ሀገረ ፡ ኢየሩ
ሳሌም ፡ ኀበ ፡ ዘሩባቤል ። ወአትሙሂ ፡ ጽሒፈክሙ ፡ አምጽኡ ፡ ሊተ ፡ እመጻሕ
ፍተ ፡ ነቢያት ፡ ቅዱሳን ፡ ዘኢመጽኡ ፡ ኀቤነ ፡ ቀዲሙ ፡ በዘመነ ፡ አበዊነ ፡ ወን
ሥኡ ፡ ፳ወ፪፻ተ ፡ ዲናረ ፡ ወርቅ፡ለስንቅክሙ ። ወ፪፻ት ፡ ዲናረ፡ ወርቅ ፡ ይኩንክ
ሙ ፡ አምኃ ፡ ዘሩባቤል ፡ ከመ ፡ ትርከቡ ፡ ሞገሰ ፡ ቅድሜሁ፡ ፳ወ፪ቱ፪፡ ለፍኖት
ክሙ ፡ ወእምዝ ፡ ነሢአሙ ፡ ሖሩ ፡ አበዊነ ፡ ሀገረ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ወበጽሑ ፡ ኀ
በ ፡ ዘሩባቤል ፡ ንጉሥ ፡ ወተራከቡ ፡ በሰላም ፡ ምስለ ፡ ደቂቀ ፡ ነቢያት ፡ ትሩፋን
ወአርአይዎሙ ፡ መጻሕፍተ ፡ ነቢያት ፡ ዘመጽኡ ፡ ውስተ ፡ ሀገርነ ፡ እምቅድመ
ዘሩባቤል ፡ ወውእቶሙ ፡ አርዓይዎሙ ፡ መጻሕፍተ ፡ ትሩፋን ፡ ዘኢመጽኡ ፡ እ
ምቅድመ ፡ ዝ። አምጽኡ ፡ ትንቢተ ፡ ሕዝቅኤል ፡ ወመጽሐፈ ፡ ኢሳይያስ ፡ ወኤ
ርምያስ ፡ ነቢይ ። ወዘንተ ፡ መጽሐፈ ፡ እሂዞሙ ፡ አበዊነ ፡ ተመይጡ ፡ እምሀገ
ረ ፡ ኢየሩሳሌም፡ በዘመነ ፡ መንግሥቱ ፡ ለዘሩባቤል ። እንግዲህ ፡ ይህን ፡ ጽፈው
ያቆዩልን ፡ አባቶቻችን ፡ ምስክር፡እንዲሆነን ፡ ነበር ። እንግዴህ ፡ በአባ ፡ ጋስፓሪ
ን ፡ ቃል ፡እንግባለው ፡ እንጅ፡ሐሰት ፡ ከሆነ፡ሐሰት ፡ ለምን ፡ ከቤተ፡ክርስቲያናች

፳፯ ፡ ዳባልቅ ፡
፳፰ ፡ ስህ ፡ ታቡክ ፡
፳፱ ፡ ባሕኑና ፡
፴ ፡ ዓዲ ፡ ገዛይ ፡
፴፩ ፡ ዓዲ ፡ አምባ ፡
፴፪ ፡ ቤተ ፡ ኤልያስ ፡
፴፫ ፡ ሰጐት ፡
፴፬ ፡ ምሬና ፡
፴፭ ፡ ደምበበያ ፡
፴፮ ፡ ሰገሞ ፡
፴፯ ፡ ላስሶ ፡
፴፰ ፡ ሰንኮቤት ፡
፴፱ ፡ ሰግላሜን ፡
፵ ፡ ሐምቦራ ፡
፵፩ ፡ ቈጸሎ ፡
፵፪ ፡ ሐውዜና ፡
፵፫ ፡ ዓድ ፡ መርን ፡
፵፬ ፡ ዐድ ፡ ቅኔ ፡
፵፭ ፡ ሐዲስዓድ ፡
፵፮ ፡ ባርዝላ ፡
፵፯ ፡ አፅሚሐርማዝ ፡
፵፰ ፡ እንኩዔላ ፡
፵፱ ፡ ዓድሐንዝ ፡
፶ ፡ ዕንባቱንቂ ፡
፶፩ ፡ ኰዅሒ ፡
፶፪ ፡ ዓዲ ፡ ገርማጥ ፡
፶፫ ፡ ዓዲ፡ደቂ፡ዳዊ፡
፶፬ ፡ እክልትና ፡
፶፭ ፡ ዓድ ፡ ምልያ ፡
፶፮ ፡ ቀጠጥ፡ እክሊ፡
፶፯ ፡ ሐንክሰቲ ፡
፶፰ ፡ ማይ ፡ ብዋክ ፡
፶፱ ፡ ዓድ ፡ ስዮ ፡
፷ ፡ ድራ ፡
፷፩ ፡ አምኮ ፡
፷፪ ፡ ድቡራ ፡
፷፫ ፡ ካባኑት ፡
፷፬ ፡ ማይሰዪ ፡
፷፭ ፡ ዓድ ፡ ጽሕሎ ፡
፷፮ ፡ ምላዞ ፡
፷፯ ፡ ወርናዕሌ ፡
፷፰ ፡ ዕድጠፈረት ፡
፷፱ ፡ ይቡሳ ፡
፸ ፡ ምናድቅ ፡
፸፩ ፡ ዝባንዕገለ ፡
፸፪ ፡ ገብገብ ፡
፸፫ ፡ ዓድ ፡ ጸሐፊ ፡
፸፬ ፡ ፍልፍሊ ፡
፸፭ ፡ ማይ ፡ ጸዓዳ ፡
፸፮ ፡ ማይ ፡ ዘግራ ፡
፸፯ ፡ ዓድ ፡ መሠረት
፸፰ ፡ ዓድ ፡ ሥዩም ፡
፸፱ ፡ ዓድ ፡ ሐንከራ፡
፹ ፡ ዓድ ፡ ራዛ ፡
፹፩ ፡ ጋቅማ ፡
፹፪ ፡ ጸሊም ፡ ቤት ፡
፹፫ ፡ ዓቃቢ ፡ መርዋ
፹፬ ፡ ዓዲ ፡ ዋጠት ፡
፹፭ ፡ ቤተ ፡ ዮሐንስ፡
፹፮ ፡ እውልያ ፡
፹፯ ፡ ኮዳ ፡
፹፰ ፡ ጽላዕሎ ፡
፹፱ ፡ ሂላ ፡
፺ ፡ ወልታ ፡ ወርቂ
፺፩ ፡ ግሙዕ ፡
፺፪ ፡ ብዕዛ ፡
፺፫ ፡ ቤተ ፡ ገበዝ ፡
፺፬ ፡ ዓድ ፡ እርጉዲ፡
፺፭ ፡ ፃኢ ፡
፺፮ ፡ ብዞት ፡
፺፯ ፡ መደጌ፡ብዘፈራ
፺፰ ፡ ዓዲ ፡ አበዘ ፡
፺፱ ፡ ዓዲ ፡ እታይ ፡
፻ ፡ አዲጐሊ ፡
፻፩ ፡ ግዝግዝያ ፡
፻፪ ፡ ማይ ፡ ወይን ፡
፻፫ ፡ አባሳጌ ፡
፻፬ ፡ ዓጺ ፡
፻፭ ፡ ታዕካ ፡ ማርያም፡
፻፮ ፡ ሳውኒ ፡
፻፯ ፡ ዓዲ ፡ ደጊቡ ፡
፻፰ ፡ ዓዲ፡ አድኅኖ
፻፱ ፡ ማይ፡ ምውት ፡
፻፲ ፡ ማይ ፡ ጋኢ ፡
፻፲፩ ፡ ዓዲ ፡ ግብድ ፡
፻፲፪ ፡ ሰመማ ፡
፻፲፫ ፡ ማይ ፡ ጣፋት ፡
፻፲፬ ፡ ዓዲ ፡ ንቡረ ፡ ዕድ፡
፻፲፭ ፡ ዅሉ ፡ ፈርሃ ፡ በዘፈራ
፻፲፮ ፡ ቡር ፡ ማዕያ ፡
፻፲፯ ፡ መዞት ፡
፻፲፰ ፡ ስንፍቲ ፡

ያሉትን ፡ ቀኖች ፡ ሲቆጥሩ ፡ ልክ ፡ ፫፻፷፭ ፡ ብቻ ፡ ይገኛል ፡ ስለዚህ ፡ የዓለም ፡ ሊቃውንቶች ፡ በክብ፡ ሜትርና ፡ በቡሶል ፡ በዙሪያም ፡ ፫፻፷፭ ፡ ነጥብ ፡ ይገኛል ። ፲፪ኛም ፡ ዛሬ ፡ የሰለጠኑት ፡ ጠቢባን ፡ ሰዓት ፡ ሠሪዎች ፡ በሚሠሩት ፡ ሰዓት ፡ እንደሚታየው ፡ ዋናዪቱ፡ ቈጣሪ ፡ ፳፬ቱን ፡ ደቂቅ ፡ ስትቆጥር ፡ ደቂቃ ፡ ቆጣሪዋ ፡ በዙሪያዋ ፡ ያሉትን ፡ ፳ውን ፡ ደቂቃ፡ ታደርሳለች፡ እንደዚህ ፡ እያለች፡ እስከ ፡ ፮ት ፡ ሰዓት ፡ ፮ት ፡ ፳ ፡ ፫፻፷፭ ፡ ደግሞ ፡ እንደ ፡ ዚሁ ፡ እስከ ፡ ፲፪ቱ ፡ ሰዓት ፡ ፫፻፷፭ ፡ ሲደመር ፡ ፯፻፴ ፡ ይሆናል ፡ ይህን ፡ ለ፳ ፡ ሲከፈል ፡ ፲፪ ፡ ይሆናል ፡ ፲፪ቱ ፡ በ፴ ፡ ሲበዛ ፡ ፫፻፷፭ ፡ ይሆናል። ከላይም ፡ ፯፻፴ ፡ ያልነውን ፡ በዳዊት ፡ አምባ ፡ ስንመዝነው ፡ ዕዮን ፡ በኢትዮጵያ ፡ ፊደል ፡ ፀ፡ ፯፻፡የ፡ ፮፡ ኑ፡ ፴፡ ድምር ፡ ፯፻፴ ፡ ይሆናል ፡ ከዚሁ ፡ ለሁለት ፡ ስትከፍለው ፡ ፫፻፷፭ ፡ ፫፻፷፭ ፡ ይደርሳል ፡ ይህን ፡ ፫፻፷፭ ፡ በመሬቱ ፡ ላይ ፡ ትእምርተ ፡ መስቀል ፡ ዘርግተህ ፡ ባ፬ቱ፡ ማዕዝን ፡ ስትመድበው ፮፡ ፮ ፡ ይደርሳል ፡ ፬ት ፡ ጊዜ ፡ ፮ ፡ ፫፻፷፭ ፡ ይሆናል ፡ ደግሞ ፡ ፫፻፷፭ውን ፡ በዙሪያው ፮፡ ፮ ፡ ስትመድበው ፡ ልክ ፡ ፬ት ፡ ጊዜ ፡ ፮፡ ፫፻፷፭ ፡ ይሆናል ።




የኢትዮጵያ ፡ ፊደሎች ፡ የአዳምና ፡ የመላእክት ፡ መነጋገሪያ ፡ ነበሩ ፡ ብየ ፡ ስናገር ፡ ባ፩ድ ፡ ፩ድ ፡ ሰዎች ፡ ዘንድ ፡ ቃል ፡ ስጋ ፡ አልሆነም፡ ብየ፡ እንደተናገኩ አድርገው ፡ ስለሚቆጥሩት ፡ የግዕዝ ፡ ፊደሎችና ፡ ፯ቱ ፡ ዕለታት ፡ ተባብረው ፡ በወር፡ እየተሠፈሩ፡ ያመቱ፡ ከመንፈቅ ፡ ፫፻፷ቱ ፡ በምሥራቅ ፡ ተመዝነው ፡ የተጻፉትን ፡ አስተዋይ ፡ ሲመለከት ፡ ፭፮ ፡ እሁድ ፡ ይገኛል ። እሁድ ፡ ስለተባለ ፡ መለያው ፡ ለየራሳቸው ፡ ቊጥር ፡ ለ፯ቱም ፡ ፊደሎች፡ እንዳላቸው ፡ በሰንጠረዥ፡ የተጻፈውን፡ አስተውሎ፡ መመልከት፡ ነው ።

ያዕቅብ ፡ ዘመን ፡ ይመስለኛል ፡ ሰጥተዋልና ፡ ) የሐስታቸው ፡ ብዛት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ባዬ ፡ ዘርዓ ፡ ያዕቆብ ፡ ዘመን፡ ካቶሊካውያን ፡ ኢትዮጵያን፡አረገጡም። መልክተኞችን ፡ አገቡዋቸው ።

«ከዚህም፡ በኋላ፡ አስተርጓሚአቸው ፡ ሳፒቶንን ፡ አደረጉላቸው፡ የወሰዱት፡ አስተርጓሚው፡ ሳይሰማቸው፡ ስለቀረ። አባቴ ፡ እምነቱም ፡ካረቢኛ ፡ በስተቀር ፡ ኢጣልያና ፡ ያውሮፕ ፡ ቋንቋ ፡ አያውቁም ፡ ነበርና፡ ካርዲናል፡ በርናቦ፡ ባለማወ ቃቸው ፡ አዘኑ ።

ከዚህም፡ በኋላ፡ አባቴ፡ እምነቱ፡ ይህን፡ መልእክት፡ ወደ፡ አባታችን፡ ጻፉ ። ተጽፈት ፡ አመ ፡ ፳ ፡ ወ ፡ ፱ ፡ ለየካቲት ፡ በዕለተ ፡ ሰኑይ ፡ በ፲ ፡ ወ ፡ ፰ ፡ ፻ ፡ ፶ ወ፩ ፡ ዓ ፡ ም ፡ አ፡ አቡየ ፡ ክቡር ፡ በኵሉ ፡ ወሐዋርያ ፡ ያዕቆብ ፡ ሰላም፡ ለከ ፡ ሰ ላመ ፡ እግዚአብ ፡ ወፍቅራ ፡ ለእግዝትን ፡ የሃሉ ፡ ምስሌከ ፡ ከጅዳ ፡ እስከ ፡ ሰዊ ስ ፡ በደህና ፡ መድረሳችንን ፡ ጽፌ ፡ እንዲደርስዎ ፡ በፈረንሳዊ ፡ መርከብ ፡ ሰጥቼ ነበርኩ ። ከስዊዝም ፡ ወደ ፡ እስክንድርያ ፡ ኮንሱል ፡ ጄኔራል ፡ ሳፒቶ ፡ በደህና ፡ አደረሱን ። ወደ ፡ ላዛርስቲ ፡ ቤት ፡ ገባን ።

፫ሌሊት ፡ በዚያው ፡ አደርን ፡ ኮንሱል ፡ ቢነግሩአቸው ፡ ነው ። የተረዱ ፡ አ ቡነ ፡ ፔርፒቶንም ፡ በመንገድ ፡ አገኟቸው ፡ መልክቱንም ፡ ኮንሱል ፡ ጀኔራል ከእስክንድርያ ፡ እስከ ፡ ሲቢታኬያ ፡ እስክንድር ፡ ለመርከቡ፡ ዋጋን ፡ ሰጡልን ። ለምግባችን ፡ ግን ፡ እኛ ፡ ከፈለን ። በየካቲት ፡ በ፪ኛ ፡ ሌሊት ፡ ወደሮም ፡ ደረሰን በእንግዳ ፡ ቤት ፡ አደረን ። በነጋውም ፡ አቡነ ፡ ዮሴፍን ፡ ስናስፈልግ፡ ዋለን ። አ ላገኘናቸውም። ለጥሩስን ፡ ይጂ ፡ ወደ ፡ ፕሮፓጋንዳ ፡ ሄዱ፡ ወረቀቱንም ፡ ለካር ዲናል ፡ በርናቦ ፡ ሰጠሁዎ ፡ በመልካም ፡ ፊት ፡ ተቀበሉን ። አቡነ ፡ ዮሴፍን ፡ አ ስፈልጌ፡ እስክሰደው፡ድረስ፡በዚያ፡ ባላችሁበት፡ ቆዩ፡ አሉን፡ ከዚያም ፡ ወጥተን ፡ ወደ ፡ ላዛርስቲ ፡ የማኅበር ፡ ቤት ፡ ገባን ። የአቡነ ፡ ዮሐንስን ፡ ወረቄት ፡ ሰጠን ፡ አቡነ ፡ ዮሴፍን ፡ አስፈልጉልን ፡ አልን ። እነዚያም ፡ ፈልገው ፡ አመጡልን ፡ እጅግ ፡ ደስ፡ አለኝ። ሁለታችን፡ ወደ፡ ካርዲናል፡ ሄደን ። ምግብንም ፡ ልብስንም ፡ ስፍራንም ፤ እንደ፡ እውቀትህ፡ አድርግላቸው፡ አሉ። ሁሉንም፡ አደረጉልን ፡ የም ነግርዎ ፡ ጉዳይ ፡ አለኝ ፡ ብልዎ ፡ በወረቀት ፡ ጻፈው ፡ አቡነ ፡ ሳፒቶ ፡ በኢጣልያ ቋንቋ ፡ ገልብጠው ፡ ይሰጡኛል ፡ አሉኝ ። ሊታተሙ ፡ የወሰድኋቸው ፡ መጻሕፍ ቶች ፡ ለርሳቸው ፡ ስጥ ፡ አሉኝ ፡ ሰጠሁ ።

እንዳሉኝም ፡ ቃሉን ፡ ጻሑፍ ፡ እርሳቸው ፡ አሳምረው ፡ ገለበጡት ። ካርዲ ናሎችና ፡ ጉባኤም ፡ ፓፓም ፡ ሁሉ ፡ አመሰገኑት። አቡነ ፡ ሴዮፍ ፡ ከሁሉ ፡ ታላላ ቆች ፡ ሰዎች ፡ ጋራ ፡ አገናኙኝ። ብልሃቱን ፡ ያውቁበታልና ፡ እርሳቸውን ፡ ባናገ ኙ፡ ይቸግረን፡ ነበር። የተገናኘናቸው፡ ተላላቅ፡ ሰዎች ፡ ነገራችንን ፡ አመሰገኑት።

ብፁዕ ፡ ፓፓም ፡ መልክተኞች ፡ ከሳፒቶ ፡ ጋራ ፡ ይምጡ ፡ እገናኛለሁ ፡ ብ ለዋል ፡ ልጅ ፡ ጣቃዬ ፡ እንደወታደር ፡ ለብሶ፡ ቢተዋውን ፡ አግብቶ፡ አንበሳ ፡ ለ ምዱን ፡ ለብሶ ፡ ሾተሉንም ፡ ታጥቆ ፡ ነበር ፡ እኔም ፡ እንዳገራችን ፡ ቄስ ፡ ጋብር ም ፡ (ሎሌ ፡ )እንደ ፡ ትርኩ ፡ ለብሰን ፡ ገባን ፤ ተምበርከክንም ፡ እግርዎን፡ ሳምን፡ አቡነ ፡ ዮሴፍ ፡ በፊታችን ፡ ሆነው ፡ ወረቀቱን ፡ ሰጡ ፡ በመልካም ፡ ተቀበሉን ፡ የሃይማኖት ፡ ነገር ፡ ቢሆን ፡ ነው ፡ እኔን ፡ የሰደዱኝ ፡

ንጉሥ ፡ ንጉሤም ፡ ይህንን ፡ መልእክት ፡ ከቅዱስ ፡ ፓፓ ፡ እግር ፡ ታች ፡ ል ናኖር ፡ ሰደዱን ፡

የሥዕሉቲቱም ፡ መልክት ፡ በማይጠፉ ፡ አስደርገው ፡ ትሰቅልልኝ ፡ ብለው አልሁ ።

በቅዱስ ፡ ጴጥሮስ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በትልቅ ፡ አጀብና ፡ ግርማ ፡ እኒያ፡ የሃይማኖት ፡ ጅግና ፡ የሆኑት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ልጅ ፡ አባ ፡ ገብረ ፡ ሚካኤል ፡ በመላው ፡ ዓለም ፡ «ብፁዕ»ተብለው ፡ እንዲከበሩና ፡ እንዲጠሩ ፡ አዘዙ ።

## ጸሎት ።

ኦ፡ ብፁዕ ፡ ገብረ ፡ ሚካኤል ፡ ዘከአውከ ፡ ደመከ፡ ወመጦከ፡ ነፍስከ፡ በእንተ ሃይማኖትከ ፡ ወተፀገስከ ፡ ሞተ ፡ መሪረ ፡ በእንተ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት፡ሰአል ፡ በእንቲአነ ፡ ኃበ ፡ እግዚአብሔር ፡ የሀበነ ፡ ለነኒ ፡ ዘከመዝ ፡ እምነተ፡ወኃይለ ፡ ከመ ፡ ንሕነኒ ፡ ናጥብዕ ፡ በእንተ ፡ ሃይማኖትነ ፡ ወንዕቀብ፡ዘእንበለ፡ኃፍረት ፡ ወዘእንበለ ፡ ፍርሀት ።

ወዓዲ ፡ ተዘከር ፡ ወጸሊ ፡ በእንተ ፡ ኵሉ ፡ ሕዝበ ፡ ብሔርከ ፡ ከመ፡እግዚአ፡ ያርኁ ፡ ወይክዐው ፡ መዝገበ ፡ በረከቱ ፡ ላዕሌሆሙ ፡ ወይፈኑ ፡ ዲቤሆሙ ፡ ብርሃነ ፡ ዚአሁ ፡ ከመ ፡ ይርከቡ ፡ አማናዌ ፡ ፍኖተ ፡ ብርሃን ፡ ወይትመየጡ ፡ ኀበ ፡መንበሩ ፡ ለሊቀ ፡ ሐዋርያት ፡ ጴጥሮስ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ አሐደ ፡ መርዔተ፡ለአሐዱ፡ ኖላዊ ። አሜን ።

---

ለይትነተም ። ጴጥሮስ ፡ ፍን ፡ ሊይርድ ፡ ሀየንተ ፡ ርእሰ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ።

በፍቲካን ፡ እመ ፡ ፳፫ ፡ ለጥር ፡ ፲፱፻፵፪ ።

ይህን ፡ አስደናቂ ፡ ታሪክ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ታስተውላለች ፡



አጼ ፡ ዮሐንስ ፡ ከሡሐጢ ፡ የተመለሱበት ፡ ምክንያት ፡ የሮማ ፡ ልዑካን ፡ የነ ገሥታቱን ፡ ዓዋጅ ፡ እየጣሱ ፡ ሲሰብኩ ፡ በተገኙ ፡ ቁጥር ፡ በጐንደር ፡ ከተማ ፡ ላይ ፡ ቅጣታቸውን ፡ ይቀበሉ ፡ ስለ ፡ ነበር ፤ የወገኖቻቸውን፡ በቀል ፡ ለመከፈል፡ ጐንደርን ፡ ለማስጠፋት ፡ ብዙ ፡ ያስቡ ፡ ስለነበር ፡ አጼ ፡ ዮሐንስ፡ ወደ፡ሡሐጢ፡ ለጦርነት ፡ ሲወርዱ ፡ ጊዜ ፡ ስለገጠማቸው ፡ ደርቡሽን ፡ ጠቅሰው ፡ እያደፋፈሩ፡ አምጥተው ፡ ከንጉሥ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትም ፡ አዋተው ፡ የጐንደርንም ፡ሕዝበ፡ ክርስቲያን ፡ አሳርደው ፡ ከተማውንም ፡ አጠፍተው ፡ በጐንደር ፡ ላይ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ መከራ ፡ ስለወደቀበት ፡ የጐንደር ፡ ሊቃውንት ፡ ወደ ፡ አጼ ፡ ዮሐንስ ፡ የ ጻፉት ፡ ደብዳቤ ፡ መዝ ፡ ፸፰ ፩ እግዚአ ፡ ቦኡ ፡ አሕዛብ ፡ ውስተ ፡ ርስትከ ፤

ወአርኰሱ፡ጽርሐ፡ መቅደስከ ፤ ወረሰይዋ ፡ ለጐንደር ፡ ከመ ፡ ልገተ ፡ ዓቃቤ ፡ ቀምሕ ፡ ፪ ወረሰዩ ፡ አብድንቲሆሙ ፡ ለአገብርቲከ ፡ መብልዓ ፡ ለአዕዋፈ ፡ ሰማ ይ ። ወሥጋሆሙ ፡ ለጻድቃኒከ ፡ ለዓራዊተ ፡ ገዳም ፤ ፫ ወከዓዉ ፡ ደሞሙ ፡ ከመ ፡ ማይ ፡ ዓውዳ ፡ ለጐንደር ፡ ወኃጥኡ ፡ ዘይቀብሮሙ ። ፬ ወኮነ ፡ ጽዕለተ ፡ ለጎር ን ። ሰሐቀ ፡ ወስላቀ ፡ ለአድያሚነ ። ፭ እስከ ፡ ማእዜኑ ፡ እግዚኦ ፡ ትትመዓዕ ፡ ለዝሉፉ ፡ ወይነድድ ፡ ከመ ፡ እሳት ፡ ቅንዓትከ ። ከዓው ፡ መዓተከ ፡ ላዕለ ፡ አሕ ዛብ ፡ እለ ፡ ኢየአምሩከ ።

የተላከ ፡ ከብላታ ፡ ገብረ ፡ እግዚአብሔር ፤ ይድረስ ፡ ከብላታ ፡ ጳውሎስ ፡ እንዴት ፡ አሉ ፡ እጅጉን ፡ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይመስገን ፡ ደህና ፡ ነኝ ፡ በሐረርጌ ፡ ሳለሁ ፡ ካንድ ፡ ካቶሊካዊ በከረን ፡ አገር ፡ በሺህ ፡ ፰፻፶፯ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ አባ ፡ ዮሐንስ ፡ የካቶሊክ ፡ መነኰሴ ፡ ያተሙት ፡ ትንሽ ፡ መጽሐፍ ፡ አየሁ ፡ መጽሐፉን ፡ ባስተውለው ፡ እጅግ ፡ የሚያስደንቅ ፡ ነገር ፡ አገኘሁበት ፡ እንደምን ፡ ቢሉ ፡ አንድ ፡ ካቶሊካዊ ፡ እስክንድርያ ፡ ገብቶ ፡ ከአንድ ፡ ግብፃዊ ፡ ቄስ ፡ ጋራ ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ተዋወቀና ፡ የሃይማኖት፡ ነገር ፡ ሲከራከሩ፡ ካቶሊካዊው፡ ረታ፡ ግብፃዊ ፡ ተረታ ፡ ይላል ፡ ቢረታ ፡ ደግሞ ፡ ቆሞስም ፡ ደብተራም ፡ ቢያመጣ ፡ በክርክር ፡ እየተረቱ ፡ ገቡ ፡ የሚል ፡ አገኘሁበት ፡ መጽሐፉን ፡ እንዳልከልዎ ፡ ባለቤቱ ፡ እሺ ፡ ብሎ ፡ አይሰጠኝምና ፡ ይኸው ፡ ግብጻዊ ፡ ተረታ ፡ የተባለበትን ፡ ጥይቅና ፡ ምላሽ ፡ ሁሉ ፡ በደብተር ፡ አስጽፌ ፡ ሰድጄልዎታለሁና ፡ ከብሉይ ፡ ከሐዲስ ፡ ከሊቃውንት ፡ የተቀደሱች ፡ እርቶ ፡ ዶክሳዊት ሃይማኖት ፡ አውጥተው ፡ ይላኩልኝ ፡ በ፲፱፻፶፯ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ በዘመነ ፡ ዮሐንስ ፡ ኅዳር ፡ ፲፯ ፡ ቀን ፡ ሐረርጌ ፡ ከተማ ፡ ተጻፈ ፡

ይድረስ ፡ ከብላታ ፡ ገብረ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዴት ፡ አለህ ፡ እጅጉን ፡ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይመስገን ፡ ደህና ፡ ነኝ ፡ የላክህልኝ ፡ የሃይማኖት ፡ ክርክር ፡ ያለበት ፡ ደብተር ፡ ደረሰልኝ ፡ ካቶሊኮች ፡ እውነትን ፡ በሐሠት ፡ ለመለወጥ ፡ አይፈሩም ፡ ስለምን ፡ ቢሉ ፡ የመንግሥት ፡ ሰማያትን ፡ መክፈቻ ፡ ይዘናልና ፡ ምናለብን ፡ ይላሉ ፡ ጌታ ፡ በቅዱስ ፡ ማቴዎስ ፡ የተናገረው ፡ ይፈጸምባቸው ፡ ዘንድም ፡ ፳፫ ፡ ቁ ፡ ፲፫ ፡ ወዮላችሁ ፡ እላንት ፡ ጸሐፎች ፡ ፈሪሳውያንም፡ ግብዞች ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያትን ፡ በሰው ፡ ፊት ፡ ትዘጋላችሁና ፡ እላንት ፡ አትገቡምና ፡ የሚገቡትንም ፡ ይገቡ ፡ ዘንድ ፡ አትተውም፡ ደግሞ፡ ሉቃስ ፡ ም ፡ ፲፩ ፡ ቁ ፡ ፶፪ ፡ ወዮላችሁ ፡ እላንት ፡ የኦሪት ፡ ሰዎች ፡ የእውቀት ፡ መክፈቻ ፡ ወስዳችኋልና ፡ እናንተም ፡ አልገባችሁ ፡ የሚገቡትንም ፡ ከለከላችሁ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ነግሮባቸዋልና ፡ ሐሠት ፡ ለመናገር ፡ አይመለሱም ፡

